# DDU TIMES

*Volume 2 Issue 3/2016*

*DDU TIMES*
*March 2016*

## ጤና ለሁለንተናዊ ለውጥና እድገት ግብዓትና ግብ መሆኑን በመረዳት በጤናው ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ ባለሞያዎች ኃላፊነታቸውን በሀገራዊ ስሜትና ብቃት መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ የጤና ሚኒስትር ሚኒስቴር ዲዔታ ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ አስገነዘቡ፡፡

**Dire Dawa University**

News letter produced by International & Public Relation Directorates Office

*Visit us online*

*Inside this issue:*

## የውስጥ ገፆች

ጤና ለሁለንተናዊ ለውጥና እድገት ግብዓትና ግብ መሆኑን የጤና ሚኒስትር ሚኒስቴር ዲዔታ ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ አስገነዘቡ፡፡

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታል በዛሬው እለት ተመርቆ በከፊል ለአገልግሎት ክፍት ሆነ፡፡

በዩኒቨርሲቲያችን ሲካሄድ የነበረው 9ኛው ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ተጠናቀቀ፡፡

በ8ኛው ዙር ሀገር አቀፍ የምስለ ችሎት ውድድር የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ 4 ዋንጫዎችን በማግኘት አሸናፊ ሆነ፡፡

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛውን ዙር ሀገር አቀፍ የመውጫ ፈተና መስጠት መጀመሩን አስታወቀ፡፡



ሚኒስትሩ የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ በዛሬው እለት በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጁ ለ7ኛ ዙር እንዲሁም በማኅበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ተማሪዎችን ባስመረቀበት ስነ-ስርዓት ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ሀገራችን ወደ ብልፅግናው ማማ ላይ የምታደርገውን ግስጋሴ ለማሳካት ጤና ለሁሉም እንቅስቃሴያችን መሠረት ነው፡፡

ወደ ገጽ.... 3 የዞረ

## በዩኒቨርሲቲያችን ሲካሄድ የነበረው 9ኛው ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ተጠናቀቀ፡፡



በዩኒቨርሲቲው የምርምር ህትመት፣ ስነዳና ስርጭት ዳይሬክቶሬት አዘጋጅነት “Synergizinig Business, Health and Technology & Engineering for Sustainable Development” በሚል መሪ ቃል ሲካሄድ የቆየው 9ኛው ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ተጠናቀቀ፡፡

ወደ ገጽ.... 4 የዞረ

## የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታል በዛሬው እለት ተመርቆ በከፊል ለአገልግሎት ክፍት ሆነ፡፡



በ2000 ዓ.ም ላይ ግንባታው የተጀመረው የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታል መሀል ላይ በተፈጠሩ የተለያዩ ችግሮች ሳቢያ ግንባታው ሳይጠናቀቅ ከ16 ዓመት በላይ ፈጅቷል ፡፡ ሆስፒታሉን በ2011 ዓ.ም ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በባለቤትነት ተረክቦት ቀሪ ግንባታዎችን አጠናቆና አስፈላጊ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራዎችን በማከናወን በዛሬው እለት በይፋ ተመርቆ ለአገልግለት ክፍት እንዲሆን አድርጓል፡፡

ወደ ገጽ.... 3 የዞረ

## በ8ኛው ዙር ሀገር አቀፍ የምስለ ችሎት ውድድር የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ 4 ዋንጫዎችን በማግኘት አሸናፊ ሆነ፡፡



ወደ ገጽ.... 5 የዞረ

# Collaboration with DDU

**Vision of DD**

Dire Dawa University aspires to be a premium choice in Ethiopia and among the top ten Applied Science Universities in Africa by 2030.






Dire Dawa University with Dialgues En Humanite, an organization based in France, and the Dire Dawa Administration and the French embassy in Ethiopia held a one day even with the theme “Building bridges to live together”. The Event involved a half-day panel discussion on food security with panelists from Ethiopia and France presenting their organization experience on the issue. The afternoon session included screening of a documentary called “The Art of Friendship” and exhibition of handmade crafts by the delegate from Mali.








Dire Dawa University in collaboration with the Embassy of Canada in Ethiopia held one-day workshop on Scholarship opportunities in Canada. A team from the embassy came to the university to present the students and the staff on specific universities where scholarship is offered and related visa acquiring process. In a follow up to this event, a team from Dire Dawa University travelled to the Canada embassy in Addis Ababa and attended a networking event where more than 20 canadian university delegates were present. The team held a productive partnership initiation discussion with the Canadian universities whose thematic focus aligns with the Dire Dawa University.



**Mission of DDU**

To produce competent graduates, problem solving research and technology output and provide demand driven community engagement through fostering an international academic environment enriched with democratic values thereby supporting realization of the country's vision.

ከገጽ 1.... የዞረ

## ጤና ለሁሉም ...







"ጤና ለሁለንተናዊ ለውጥ መምጣት ግብዓትና ግብ ነው" ያሉት ሚኒስትር ዲዔታው ዶ/ር ደረጀ በጤናው ዘርፍ የምናደርገውን ኢንቨስትመንት እያጠናከርን ወደ ምንመኘው እድገት ላይ መድረስ ይጠበቅብናል።

በዚህ ረገድም በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሞያዎች የማይተካ ሚና አላቸው ያሉት ሚኒስትር ዲዔታው በጤናው ዘርፍ ላይ የሚሠማሩ ባለሞያዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በትልቅ ሀገራዊ ስሜትና በብቃት መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ አስገንዝበዋል።

በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ አደም በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው በጤናው ዘርፍ የሚፈለገው እድግት እንዲመዘገብ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ መሆናቸውንና በዚህም የተለያዩ ለውጦችን መመዝገብ መቻሉን ተናግረዋል።

በተለይም በጤናው ዘርፍ ብቁና የሠለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አንፃር ዩኒቨርሲቲው በጤና ሳይንስ ኮሌጁ በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ተማሪዎችን እያስተማረ የሚያስምርቅ መሆኑን ጠቅሰው እነዚህ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ ሲሰማሩ ህብረተሰቡን መልካም ስነ-ምግባርን በተላበሰና የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አገልግልት መስጠት እንዲችሉ በተግባር የተደገፉ የተለያዩ ስራዎች የሚከናወኑ መሆኑን ገልፀዋል።

እንደ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ ገለፃ በዘንድሮ ዓመት በዩኒቨርሲቲው በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመውጫ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች 98.7 በመቶ ተማሪዎች ፈተናውን ማለፍ መቻላቸው ለዘርፉ የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ማሳያ ነው ብለዋል።

እነዚህ የተገኙ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች በማስቀጠል በጤናው ዘርፍ ብቁና የሰለጠነ ባለሞያዎችን በብዛትና በጥራት በማፍራት መከላከል ላይ ትኩረት ያደረገው የጤና ፖሊሲያችን እንዲሳካ ዩኒቨርሲቲው የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አረጋግጠዋል።

በዚሁ የምርቃ ስነ-ስርኣት ላይ የድሬዳዋ አስተዳደር አፈ-ጉባዔ ክብርት ወ/ሮ ፈቲሃ አደን ፣ም/አፈጉባዔ ክብርት ወ/ሮ ከሪማ አሊ ፣የድሬደዋ አስተዳደር የጤና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ፅጌረዳ ክፍሌ እና የተለያዩ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንዲሁም የተመራቂ ቤተሰቦች ተገኝተዋል።




ከገጽ 1.... የዞረ

## የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያና ሪፈራል ...



በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የጤና ሚኒስቴር ሚንስትር ዲዔታ ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ ድሬዳዋ የምስራቁ የሀገራችን ክፍል የንግድ ፣ የኢንዱስትሪ ማዕከል እንደመሆኗ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከከተማዋ እድጋጅገት ጋር የሚመጥን የጤና ተቋም ሊኖራት ግድ ይላል ብለዋል።
በዚህ ረገድም የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታል ከሚገኝበት አካባቢው አልፎ እንደ ሀገርም በጤናው ዘርፍ ትልቅ አስተዋፅዖ መወጣት የሚችል ተቋም ሆኖ የተቋቋመ መሆኑን ተናግረዋል።
ሆስፒታሉ በድሬዳዋ ከሚገኙ አጠቃላይ ሆስፒታሎች እና በሶማሌና በኦሮምያ ክልል ከሚገኙ የጤና ተቋማት በመቀናጀት በሽታን አስቀድሞ በመከላከሉ እንቅስቃሴ ላይ የራሱን የሆነ አሻራ ማሳረፍ እንደሚኖርበት ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ ተናግረዋል።
በዚሁ የምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ የተገኙት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሀር በበኩላቸው የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታል ከአስተዳደሩ ባለፈ ለአጎራባች ክልሎችና የጎረቤት አገር ህዝቦች የጤና አገልግሎት ሽፋንን የሚያሳድግ ነው።
ሆስፒታሉ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዩኒቨርሲቲው ስር ሆኖ አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ በጤናው ዘርፍ የሚደረጉ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን በብዛትም ሆነ በጥራት በመጨመር በሽታን አስቀድሞ በመከላከል ጤናው የተጠበቀና ኢንደስትሪው የሚፈልገውን አምራች ዜጋን በማፍራት ሀገራችን የጀመረችውን የተፋጠነ የልማት ጉዞ ከዳር በማድረስ እድግት እንዲመዘገብ የማድረግ አቅም ያለው ነው ብለዋል።
በዚህ ረገድ የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታሉ የጤና አገልግሎት ለድሬዳዋና ለአካባቢዋ ነዋሪ መስጠት መጀመሩ የሚኖረው ፋይዳ ዘርፈ ብዙና በህዝባችን ህይወት ላይ የሚፈጥረው በጎ ተፅዕኖ ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ አስተዳደሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጋል ብለዋል።
በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ በመገኘት የስነ-ስርዓቱን ታዳሚዎች እንኳን ደህና መጣችሁ ያሉት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ አደም በበኩለቸው ዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታሉን በ2011 ዓ.ም ተረክቦ በ500 ሚሊዮን ብር ቀሪ ሥረዎችን አጠናቆ ለምረቃ የበቃና በከፊል ሥራ ማስጀመር የተቻለ መሆኑን ጠቁመው በአሁኑ ሰዓትም ሆስፒታሉ ህሙማን ተኝተው መታከም የሚችሉባቸው 400 አልጋዎችን የያዘ መሆኑን ተናግረዋል።
በከፊል ሥራ የጀመረውን የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታሉን ቀሪ ሥራዎችን አጠናቆ በሙሉ አቅሙ አገልግሎት በመስጠት የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ሽፋን የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ በየአቅጣጫው የተጀመሩ ርብርቦች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብለዋል።
በዚህ ረገድም ሁሉም ወገን ይሄን ከሀገር አልፎ ለጎረቤት አገራት ህዝቦች ሳይቀር ጥራት ያለው ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ዘመናዊና ግዙፍ ሆስፒታል በሙሉ አቅሙ አገልግልት መስጠት እንዲችል ሁሉም ሰብአዊ ግዴታውን ሊወጣ ይገባል ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።
የድሬደዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ፅጌረዳ ክፍሌ በበኩላቸው የማስተማሪያና ሪፈራል ሆስፒታሉ በይፋ ተመርቆ በከፊል ሥራ መጀመሩ በድሬዳዋ በሚገኙ የጤና ተቋማት ላይ የተፈጠረውን መጨናነቅ በመቀነስ የነዋሪው የጤና አገልግሎት ሽፋን ያሳድጋል ሲሉ ተናግረዋል።
ቢሮው ከዩኒቨርሲቲው ጋር በመተባበር ሆስፒታሉ በሙሉ አቅሙ አገልግልት መስጠት እንዲችል የማድረጉን ሥራም በቻለው አቅም ሁሉ እገዛና ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን መወጣቱን ይቀጥላል ሲሉ አረጋግጠዋል።

በምረቃው ስነ-ስርዓቱ የተገኙ እንዳንድ የድሬዳዋ ነዋሪዎች በሰጡት አስተያየት ይሄ ግዙፍና ዘመናዊ ሪፈራል ሆስፒታል ቤታችን ደጃፍ ላይ ግንባታው ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት መሆኑ በቀጣዩ ዘመን ከበሽታ የተጠበቀን አካባቢን ከመፍጠር አንፃር ትልቅ ተስፋን የሚያጎናፅፍ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ከገጽ ... 1 የዞረ

## 9ኛው አገር አቀፍ የምርምር ኮንፈራንስ ....








"በዚህ ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ላይ በመገኘት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተማም አወል ሲሆኑ በመልዕክታቸው መምህራኖቻችን ወደ ህብረተሰቡ በመቅረብ ማኅበረሰባችን ያሉባቸውን ችግሮች በመረዳት በጥናት ላይ የተመሰረተ የመፍተሔ አቅጣጫ ማመላከት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

በምርምር ኮንፍረንሱ ላይ የዩኒቨርሲቲያችን ፕሬዝዳንት የሆኑት ዶ/ር ኡባህ አደም የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም ምርምሮችን ከቴክኖሎጂ ጋር በማቀናጀት የህብረተሰባችን ችግር መፍቻ እንዲሆኑ መስራት እንደሚገባ አስገንዝበው በዚህ ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ መሰረታዊ ችግሮችን በመለየት የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በኮንፍረንሱ ላይ ዶ/ር ሰለሞን ቢኖር የትምህርት ሚኒስቴር የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ጄኔራል 'Accreditation System of Ethiopian Research Journals: Lessons Learned and Prospects'፣ ዶ/ር ይትባረክ ተክሌ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ 'Business and Economic Strategies for Sustainable Development'፣ ፕ/ር ስለሺ ግርማ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ 'Health Innovations for Sustainable Development' እንዲሁም ፕ/ር ዳንኤል ቅጣው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲውት 'Technology Catch-Up and Window of Opportunity' በሚሉ አርዕስቶች ቁልፍ መልዕክቶቻቸውን በቅደም ተከተል አቅርበዋል፡፡

በዚህ ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ላይ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ጥናት አቅራቢዎች የጥናትና ምርምር ስራዎቻቸውን ያቀረቡ ሲሆን በኮንፍረንሱ ላይ ከ18 በላይ የሚሆኑ የምርምር ስራዎች ቀርበው አስፈላጊው ውይይት የተደረገባቸው መሆኑን የዩኒቨርሲቲው የምርምር ህትመት፣ ስነዳና ስርጭት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ሙሀመድ ቃሶ ተናግረዋል፡፡ ዶ/ር ሙሀመድ አያይዘውም የዩኒቨርሲቲያችን መምህራን በምርምርና ህትመት ዙርያ ያላቸውን ተነሳሽነት አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ለማድረግ እና ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ውጤቶች ወደማኅበረሰቡ በሚደርሱበት ሁኔታ ላይ ዳይሬክቶሬቱ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

## የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛውን ዙር ሀገር አቀፍ የመውጫ ፈተና መስጠት መጀመሩን አስታወቀ፡፡







ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዙር ሀገር አቀፍ የመውጫ ፈተና በተያዘለት መርሀግብር መሠረት መስጠት መጀመሩን የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት የሆኑት ዶ/ር መገርሳ ቃሲም ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር መገርሳ ቃሲም አያይዘው በዛሬው ዕለት 239 (ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ) የህክምናና ጤና ሳይንስ ተማሪዎች ፈተናው መውዳቸውን ገልጸዋል፡፡ ዛሬ የተሰጠው የመውጫ ፈተና ያለምንም ችግር በተያዘለት መርሀግብር መሰረት የተሰጠ መሆኑን ገልጸው ዩኒቨርሲቲው አስቀድሞ በቂ ዝግጅት ማድረጉን ነው ዶ/ር መገርሳ ያሳወቁት፡፡

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ቅበላ፣ የአካዳሚክ ሪከርድ እና አልሙኒ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ጂብሪል አብዱልቃድር እንዳሳወቁት ሀገር አቀፍ የመውጫ ፈተና ከማክሰኞ የካቲት 6/2016 ዓ.ም እስከ ፊታችን እሁድ የካቲት 11/2016 ዓ.ም ድረስ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በአጠቃላይ በ55 የትምህርት አይነቶች ፈተናው የሚሰጥ መሆኑን ገልፀው ባጠቃላይ 1,186 (አንድ ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት) ተማሪዎች ፈተናውን እንደሚወስዱ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ዶ/ር ጂብሪል አያይዘው የመውጫ ፈተናውን ለመፈተን በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በኩል በ8 የትምህርት አይነቶች ቁጥራቸው 239 (ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ) ተማሪዎች ለማስፈተን እቅድ መያዙን ገልጸው የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲን የመፈተኛ ጣቢያቸው እንዲሆን የመረጡ ከግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከሪፍትቫሊ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዲስ አበባ ሜዲካልና ቢዝነስ ኮሌጅ፣ ከሲቲ ሜዲካልና ቢዝነስ ኮሌጅ፣ ከኪያመድ ኮሌጅ እና ከሉሲ ኮሌጅ ሁለተኛውን ዙር ሀገር አቀፍ የመውጫ ፈተና በሚቀጥሉ ቀናቶች እንደሚፈተኑ አሳውቀዋል፡፡

**Dire Dawa University**

Address
P.O.B: 1362
Dire Dawa
Ethiopia

International & Public Relation Directorate:
Tele:
025-111-1501
E- mail: iproffice@ddu.edu.et

Face book: DDU

Telegram:DDU

## "በምህንድስናዊ ዘዴ የተሰላ፣ በተሞክሮዎች የታጀበ ምርምርና ትንተና" በሚል መሪ ቃል በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ውይይት ተካሄደ።







በምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት የተዘጋጀው "በምህንድስናዊ ዘዴ የተሰላ፣ በተሞክሮዎች የታጀበ ምርምርና ትንተና" በሚል መሪ ቃል በውይይቱን መርሀ-ግብር ላይ ንግግር ያደረጉት የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር መገርሳ ቃሲም የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው ምህንድስና ሰፊ የሙያ ዘርፍ እንደመሆኑ በውስጡ ብዛት ያላቸው ሌሎች የሙያ ዘርፎችን እንደሚይዝ ገልጸዋል።

ምህንድስና መሰል ተዛማጅ ጉዳዮችን በመመርመር እና ጥራትን የሚከታተል ዘርፍ መሆኑን አንስተዋል። ዩኒቨርሲቲው በምህንድስና ዘርፍ ከፍተኛ ባለሙያን በማሰልጠን በዘርፍ ያለውን ከፍተኛ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ አይነተኛ ሚና እንዳለው በምህንድስና ትምህርት ፕሮግራም ብቁ ተማሪዎችን በማሰልጠን ጊዜው የሚፈልገውን ብቁ ዜጋ በማፍራት ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በዚህ የውይይት መድረክ ላይ ተጋባዥ እንግዳ የሆኑት ኢንጂነር ባንተይሁን ትዛዙ በካናዳ ቶሮንቶ ነዋርነቱን ያደረገ የዘርፉ ተመራማሪ ለውይይቱ ተሳታፊ መምህራንና ተማሪዎች ገለጻ አድርገዋል። እንጂነር ባንተይሁን እንደገለጹት ምህንዲስና ለዘላቂ የልማት ግቦች ዋነኛ መሳሪያ መሆኑን አንስተው አገራችን የምትፈልገው የተማረ የሰው ኃይል እና ኢኮኖሚውን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለውን ዕድገት ለማምጣት እና በአርቴፊሻል ኢንተለጀንሲ በመታገዝ ውጤታማ ስራ መስራት እንደሚቻል ተናግሯል። ከተሞቻችን በዘመናዊ ምህንድስን በማዘመን አረንጓዴ ኢኮኖሚን በተሻለ በመፍጠርና በመጠቀም ዘርፉን ማሳደግ እንደሚቻል አጽኖት በመስጠት አብራርተዋል።

በመጨረሻም ከተሳታፊዎች ጥያቄዎች ተነስተው ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶበት ውይይቱ ተጠናቋል።

**Address**

POBOX: 1362
Dire Dawa University
International & Public Relation Directorate
Office Phone:- 025-1111-501
E-mail: iproffice@ddu.edu.et

ከገጽ 1.... የዞረ

### በ8ኛው ዙር ሀገር አቀፍ የምስለ ችሎት ውድድር ...





በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሚገኘው በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት በ 31 ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ሲካሔድ በነበረው በ8ኛው ዙር ሀገር አቀፍ የምስለ ችሎት ውድድር ላይ የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ 4 ዋንጫዎችን በማግኘት ውድድሩን በአንደኝነት አሸንፏል።


በውድድሩ ላይ ተማሪ ምህረት ወንድሙ ፣ ተማሪ ማህሌት ወርቅነህ እና ተማሪ ሰብለ ገሰሰ አሻናፊ በመሆን የዋንጫና የሜዳሊያ ተሸለሚ ሆነዋል ።

በ8ኛው ዙር አሸናፊ ለሆኑ ተማሪዎችና ለተማሪዎቹ አሰልጣኝ መምህር አለምሰገድ ደጀኔ የዩኒቨርሲቲያችን አመርራሮች፣ የህግ ኮሌጅ መምህራን እና ተማሪዎች በድሬዳዋ አለም ኤርፖርት በመገኘት ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል።



## በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ 60 የተጠናቀቁ የምርምር ስራዎች ቀርበው ተገመገሙ።






በዩኒቨርሲቲው የተጠናቀቁ የምርምር ስራዎች ለመገምገም የተዘጋጀውን መድረክ በንግግር የከፈቱት በዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር መገርሳ ቃሲም በዩኒቨርሲቲው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመምህራን በጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ ያላቸው ተሳትፎ ጨምሯል።

በዩኒቨርሲቲው የሚቀርቡ የምርምር ስራዎች ከወትሮው በተለየ መልኩ በቁጥርም ሆነ ከጥራት አንፃር በከፍተኛ መጠን ማሳደግ የተቻለበት ነው።

ዩኒቨርሲቲው በልየታ የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ዘርፍ የተለየ ከመሆኑ አንፃር በመምህራኖች የሚሰሩ የምርምር ስራዎች ከኢንዱስትሪ ተቋማት ባለሙያዎች እና ከሌሎች አካላት ጋር በጥምረት ተሰርተው ሃብት ማምጣት አለባችሁ በማለት አፅኖት በመስጠት አሳስበዋል።

የሚሰሩ የምርምር ሥራዎች ለህትመት በቅተው የመንግስትና የማኅበረሰቡን ችግር መፍታት እንዲችሉ ተመራማሪዎች በግልም ሆነ በጋራ ጥረታቸውን ማስቀጠል እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል።

የዩኒቨርሲቲው የምርምር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት ረ/ፕሮፌሰር ይታገሱ ስንታየሁ በበኩላቸው ለሁለት ቀናት በሚቆየውና በዳይሬክቶሬቱ አዘጋጅነት የሚካሄደው የምርምር ሥራዎች የግምገማ መድረክ ላይ ከህግ ኮሌጅ በስተቀር ሁሉም ኮሌጆች የተሳተፉበትና ከ60 በላይ የተጠናቀቁ የምርምር ስራዎች ቀርበው የሚገመገሙበት ነው ብለዋል።

## ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ማህበራዊና ልማት ኮሚሽን የሐረርጌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር የስልጠና ውል ተፈራረመ




የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ማሕበራዊና ልማት ኮሚሽን የሐረርጌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከ30 ዓመታት በላይ ልምድ ያለው አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን አጋሩ ከሆነው Catholic Relief Service ኢትዮጵያ ጋር በመሆን በበርካታ ዘርፎች በዩ.ኤስ.አይ.ዲ የተደገፈ ለአምስት አመት የሚቆይ Resilient Food Security Activity (RFSA)/Ifaa ፕሮጀክትን ተግባራዊ በማድረግ የቤተሰብ ምግብ እና ስነ-ምግብ ደህንነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን የሚሰራ ድርጅት ነው። ዩኒቨርሲቲው ከድርጅቱ ጋር የተፈራረመው ውል ከምስራቅ ሀረርጌ ወረዳዎች የተውጣጡ ሥራ አጥ ወጣቶችን በተለይም ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ላይ ያተኮረ ለ90 ቀናት (3 ወራት) የሚዘልቅ የስራ እድልን የሚፈጥር በጨርቃጨርቅና አልባሳት ክህሎት ላይ የሚያተኩር ሥልጠናን ለመስጠት ሲሆን፤ ስልጠናው በተግባር የተደገፈ እና የስራ ፈጠራ ክህሎቶችን የሚያስጨብጥ እንደሚሆን ይጠበቃል።

**Dire Dawa University**

Address
P.O.B: 1362
Dire Dawa
Ethiopia

International & Public Relation Office:
Tele:
025-111-1501
E- mail: proffice@ddu.edu.et

Face book: DDU

Telegram:DDU

## VISION

Dire Dawa University aspires to be a premium choice in Ethiopia and among the top ten Applied Science Universities in Africa by 2030.

## የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የከተሞች ገቢ ሪፎርም ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ከአራት ክልሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በከተማ መሬትና ፕላን ዘርፍና የሙያ ብቃት ማረጋገጫን አስመልክቶ ሲሰጥ የቆየው ስልጠና ተጠናቀቀ።







በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር መገርሳ ቃሲም በንግግራቸው አገራችን ያለመችውን ዕድገት ለማረጋገጥ ብሎም ከተሞችን ከተረጅነት ነፃ ለማውጣ በመሬትና መሬት ነክ ላይ ራሳቸውን በፋይናንስ ዘርፍ አቅም እንዲኖራቸው ለማስቻል የሰለጠኑ ብቁ የሆኑ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ ተናግሯል። ዶ/ር መገርሳ አያይዘው ከሀብቶች ሁሉ የላቀውን ሀብት ትርጉም ባለው ሂደት ለማዘመንና ከዘርፉ ሊገኝ የሚገባውን ገቢ ለማስገኘት ብቁ ሙያተኞች ስለሚያስፈልጉት ይህ ስልጠና መሰጠቱን ተናግረዋል። ዩኒቨርሲቲው ፍትሃዊ የሆነ የመሬት አስተዳደር እንዲኖር ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር የጀመረውን ግኑኝነት አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑንም አረጋግጠዋል።

በዚሁ የስልጠና መዝጊያ ፕሮግራም ላይ በመገኘት ለሰልጣኞቹ የስራ መመሪያ ያስተላለፉት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የከተሞች ገቢ ሪፎርም ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ዚነት ኢብራሂም በዚሁ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት በከተማ መሬት ልማትና ፕላን ዘርፍ ከአፋር፣ ከሶማሌ፣ ከሐረሪ ክልላዊ መንግስት እና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተመረጡ የዘርፉ ባለሙያዎች በአራት የስልጠና ዘርፎች ከደረጃ II እስከ V የሙያ ደረጃዎች አሰልጥኖ እና የሙያ ብቃት ምዘና ሲኦሲ ለሶስተኛ ጊዜ ከማዕከል በተላከው የስልጠና ቲኦቲ መሰረት የተዘጋጀ መሆኑን አንስተዋል። አያይዘውም ሰልጣኞች በተግባር ንድፈ-ሀሳብ የተደገፈ ስልጠና በስኬት ሰልጥነው እንዲበቁ ላበረከታችሁ አካላት በሙሉ የላቀ ምስጋናቸውን አቅርበው ከዩኒቨርሲቲው ጋር በቀጣይ በጋራ እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

በስልጠናው መርሀ ግብር ላይ የመዝግያ ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንሲቲትዩት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ገደፋዬ ባስተላለፉት መልዕክት ሰልጣኞች ለስልጠናው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በተግባርና በንድፈ-ሀሳብ የተደገፈ ስልጠና ወስዳችሁ መብቃታችሁ በከተሞች መሬት አስተዳደር ዘርፍ የሚታየውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመቅረፍ ሳይንሳዊ መርህን በመከተል የአከባቢያችሁን የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ስርዓት በማዘመን ከተሞች ያላቸውን የመሬት ሀብት በአግባቡ አውቀው በእቅድ እንዲመራና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም በስልጠናው ያገኛችሁትን ዕውቀት በመተግበር ህዝቡና መንግስት ከዘርፉ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ለማስጠበቅ በትጋት መስራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።



Dire Dawa University signed Memorandum of Action with CIHEAM - Mediterranean Agronomic Institute of Bari, based in Italy, to implement a project called “Empowering Entrepreneurial Skills in Green & Blue economy in Med and Africa region (Startup10)” which focuses on supporting local start-ups. The project, which will last for two years, is funded by The Italian Ministry of Foreign Affairs and International Cooperation (MAECI) and will be implemented by the university’s Business and Technology Incubation Center (BTIC).

## ሴት ተመራማሪዎች ሴቶች ካሉባቸው ውስብስብ ችግሮች ሊያላቅቁ አቅም ያላቸው የተግባራዊ የምርምር ሥራዎች ትኩረት ሊያደርጉባቸው ይገባል ተባለ።











በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በሴት ተመራማሪዎች እና አገር በቀል ዕውቀት ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ 17 ትልመ ጥናቶች ቀርበው የተገመገሙበትን መድረክ በንግግር የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ አደም ናቸው።

ዶ/ር ኡባህ በንግግራቸው እንደገለጹት ሴት መምህራን በምርምር ሥራዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በተለይ ዩኒቨርሲቲው ከባለፈው 3 ዓመት ወዲህ የሴት መምህራንን በምርምር ሥራዎች ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ለማሳደግ የተከናወኑ ተግባራት ውጤታማ ነበሩ ብለዋል።

"ሴት ተመራማሪዎች በዕለት ተዕለት ከሚገጥሟቸው ችግሮች ተነስተው ተግባራዊ የምርምር ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርገው ቢሠሩ ውጤታማ ይሆናሉ" ሲሉ ተናግረው እነዚህ ሥራዎች ወደ ማኅበረሰቡ ወርደውና ተተግብረው መልሰው ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ሴቶች ድርብ ኃላፊነት አለባቸው ያሉት ዶ/ር ኡባህ ሴት ተመራማሪዎች በተለይ ሴት እህቶቻቸው ካሉባቸው ውስብስብ ችግሮች ተላቀው መብታቸውና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ የአቅማቸውን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በተመሳሳይ በዚሁ መድረክ ላይ ቀርበው ከሚገመገሙት 17 ትልመ ጥናቶች መካከል ገሚሶቹ አገር በቀል ዕውቀት ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተማም አወል ተናግረዋል።

ዶ/ር ተማም ትልመ ጥናቶቹ ወደ መሬት ወርደው ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ዩኒቨርሲቲው በቻለው አቅም ሁሉ ድጋፍን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል። አገር በቀል ዕውቀቶቻችንን ከዘመናዊው ጎን ለጎን እያስኬድን ለሀገር ልማትና እድገት ልንጠቀምብት ይገባል በማለት አስገንዝበዋል።

## አለም አቀፋ የሴቶች ቀን በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ በፓናል ውይይት ተከበረ።













የፓናል ውይይት ተካፋይ ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ንግግር ያደረጉት በዩኒቨርሲቲው የሴቶችና ወጣቶች ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ እና ልዩ ፍላጎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ዝናሽ ደሳለኝ የአለም አቀፋ የሴቶች ቀን (March 8) በአለም አቀፍ ደረጃ ለ113 ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ46ኛ ጊዜ " ሴቶችን እናብቃ ሰላምና ልማትን እናረጋግጥ" በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ መሆኑን ገልፀዋል።

በዩኒቨርሲቲ ደረጃም ቀኑን በማስመልከት የፓናል ውይይት መዘጋጀቱን ጠቁመው በፓናሉ ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆን ፅሁፍ በዩኒቨርሲቲው ምሁራን ቀርቦ ውይይት የሚደረግበት መሆኑንም ተናግረዋል።

በፓናል ውይይቱ ላይ በመገኘት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ተወካይ ረ/ፕሮፌሰር ይታገሱ ስንታየሁ ሴቶች ለዘመናት በዘለቁ የተዛቡ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ሳቢያ ለተለያዩ ጫናና ጭቆናዎች ሲዳረጉ ቆይተዋል።

ይህ ደግሞ ሴቶችን ለበርካታ ውስብስብ ችግሮች በመዳረግ መብታቸው ተገፎ ከምጣኔሃባታዊው ፣ ከማኅበራዊው ተጠቃሚነት ተነፍገው እና ከፖለቲካው መድረክ የተገለው የቆዩበትን አስቸጋሪ ዘመን ለማሳለፍ ተገደዋል።

በፈረንጆቹ 1907 ዓ.ም ላይ ሴቶች በዩናይትድ ስቴስት ኦፍ አሜሪካ አደባባይ በመውጣት ተቃውማቸውን ከሰሙ በኋላ ግን ይሄው የሴቶች የመብት ጥያቄ በተቀረው የአለም ክፍልም ተሰራጭቶ ሴቶች ይድርሱባቸው የነበሩት ጫናዎችና ጭቆናዎች ቀስ በቀስ እየቀነሱ እንዲመጡ ማድረግ ተችሏል።

Dire Dawa University

Address
P.O.B: 1362
Dire Dawa
Ethiopia

International & Public Relation Office:

Tele:
025-111-1501
E- mail: profice@ddu.edu.et

Face book: DDU

Telegram:DDU

## ሦስተኛው የብዝሐነት ፎረም "በብሔራዊ ምክክርና ሰላም ግንባታ ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ" በሚል መሪ ቃል በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ተከበረ።








ፎረሙን በንግግር የከፈቱት የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ አደም ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔር ፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ በመሆኗ የብዝሐ ባህሎችና ቋንቋዎች በውስጣ አቀፋ እንድትይዝ አስችሏታል።

ይህ ፀጋ ደግሞ ብዙዎች እንዲኖራቸው የሚመኙት ግን የሌላቸው ታላቅ ፀጋ መሆኑን ተገንዝበን ለሀገር ዘላቂ ሰላም መስፈንና ለተፋጠነ ልማት ከዛም ከፍሲል ለሀገር እድግትና ለሁለንተናዊ ለውጥ መምጣት ልንጠቀምብት ይገባል።

ነው ያሉት ዶ/ር ኡባህ ታዲያ ይህንን ብዝሐነት ያጎናፀፈን ፀጋ ተገንዝብን ለታላቅ አገራዊ ፋይዳ በማዋል ዘላቂ ሰላምን በማረጋገጥ በቅጡ መጠቀም የእኛ ፋንታ ነው ብለዋል።

ብዝሐነትን በማከበር ማስተናገድ መጀመራችን አንዱ የስልጡን ህዝቦች መገለጫ ነው ያሉት ዶ/ር ኡባህ ብዝሐነት በአንድ አገር የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን ሙሉ ፍላጎት መኖሩን አንዱ ማሳያ መሆኑንም ተናግረዋል።

መስፈን አንዱ ማሳያ መሠልጠንተጠቅመን በሀገራችን ዘላቂ ሰላም በማረጋገጥ ልማትን በማፋጠን ትርጉም ያለው እድግትና ለውጥን በማስመዝገብ የህዝባችን ኑሮ እንዲሻሻል ሁላችንም የበኩላችን ድርሻ ልንወጣ ይገባል።

በልዩነታችን ውስጥ በአንድ ላይ ተዋህዶና ተቀይጦ የሚገኘውን ውብ አንድነታችን ከማጠናከር አንኳያ የምሁራን ሊወጡት የሚገባው ኃላፊነት ከሌሎች ትንሽ ከፍ ያለ ነው።

ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትም ምሁራን የተለያዩ ጠቃሚ ጥናትና ምርምር ሥራዎች በብዛትና በጥራት በማበርከት ልዩነትን የግጭትና የመጠፋፋት ምክንያት ሆነው አሁን አሁን ላይ በድንግት ብቅ ብለው የሚታዩትን ከፋፋይ ትርክቶች እንዲጠሩ ከማድረግ አንፃርም ድርብ ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል።

ምሁራኑ ይህንን ሀገራዊ ኃላፊነት አንግበው በተለይም ከቅርብ ወራት በኋላ ለማካሄድ በእቅድ ይዘን እንቅስቃሴ የጀመርንበት ብሔራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን የበኩላችንን ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል በማለት አስገንዝበዋል።

በዚሁ ፎረም ላይ ተገኝተው የፎረሙን ታዳሚዎች እንኳን ደህና መጣችሁ ያሉት በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተማም አወል በአገርአቀፉ ደረጃ የብዝሐነት ፎረምን የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ከዛሬ ሦስት ዓመት ጀምሮ አንዴም ሳይቋረጥ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ማለትም ለ3ኛ ጊዜ በማዘጋጀት እንዲከበር አድርጓል።

የአሁኑ ፎረም በዩኒቨርሲቲው ሲዘጋጅ በልዩነታችን ውስጥ ያለውን አንድነታችንን አጠናክረን የሀገራችን መፃዕድል የተቃና በድል ቱሩፋቶች የታጀበ እንዲሆን ለማድረግ ብዝሐነታችን ለአንድነታችን መጠናከር ያለውን የላቀ ጥቅም ግንዛቤ እንዲወሰድብት ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚሁ ፎረም ላይ የተለያዩ ምሁራን ብዝሐነትና አማራጭ የግጭት መፍቻ ባህላዊ የግልግል እሴቶችን የተመለከቱ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸው ፎረሙ ተጠናቋል።





**Mission of DDU**

To produce competent graduates, problem solving re-search and technology output and provide de-mand driven community engagement through fos-tering an international academic environment enriched with demo-cratic values thereby sup-porting reali-zation of the country's vision.

## ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፣ከኢትዩጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣንና ከድሬድዋ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ።







ድሬ ድዋ ዩኒቨርሲቲ በቅርስ ጥበቃ በባህል ጥናትና የቱሪዝም ልማትን ጨምሮ በታላላቅ ሀገራዊ ፍይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ በመግለጽ፤ የከተማ አስተዳደሩን የቅርስ የባህል ልማትና ቱሪዝም ዘርፋ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ዩኒቨርስቲው ከተቋማቱ ጋር በመሆን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በላቀ ደረጃ ውጤታማ ስራዎችን ለማከናወን ስምምነቱ አስፈላጊ መሆኑን የድ.ድ.ዩ የም/ቴ/ሽ ም/ል ፕሬዝዳንት ተማም አወል (ዶ/ር) ገልጸዋል። በፊርማ ስነ-ስርዓቱ ላይ የነበሩት የድሬድዋ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ ሚካኤል እንዳለ በበኩላቸው ከድ.ድ.ዩ ና የኢ.ቅ.ጥ.ባ ጋር በጋራ በመስራት በአሰተዳደሩ እየተሰሩ ላሉትና ለታቀዱ የቅርስ ጥበቃ ባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ በምርምር ቴክኖሎጅ ሽግግር እና በዘርፉ የለውጥ ተግባራትን እውን እንዲሆኑ ለማስቻል በሚደረገው ጥረት ላይ ስምምነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ገልጸዋል። በመጨረሻም የኢ.ቅ.ጥ.ባንም የተለያዩ ስራዎችን አብረን እየሰራን ቢሆንም በሰነድ በተደገፈ ውል ስራችንን መስራት የታቀደ ውጤታማ የሆነ ስራ ለማከናወን ይረዳናል ብለዋል።



Dire Dawa University college of medicine and health sciences staff have won research 264,118 USD USAID President's Malaria Initiative (PMI) grant to work on malaria in Dire Dawa. The university is among the only three African countries to win this global grant call for proposal out of more than 100 proposals submitted worldwide. As an induction to the project PMI Insight team lead by Dr. Joseph Wagman and Dr. kim lindblade have visited Dire Dawa University for four days working on the official project launch. The PMI Insight team handed over research material estimated to 5000 USD to her Excellency Dr. Ubah Adem, president of the university. Dr. Joseph have ensured that they will enhance their engagement more and do various activities to eliminate malaria in Dire Dawa adminstration and they will support Dire Dawa University in its capacity building programs. Dr. Ubah, on behalf of the university, also thanked the PMI Insight Team. She reiterated that among the main pillars of the Dire Dawa university are research and community services and therefore it will continue collaboration with different stakeholders to tackle the devastating malaria and arboviral disease in Dire Dawa administration. She added that the university is also working on malaria and arbovirus by allocating more than one million Birr from its own budget to its researchers through competitive call for proposal.

## Address

POBOX: 1362
Dire Dawa University
International & Public Relation Directorate
Office Phone:- 025-1111-501
E-mail: iproffice@ddu.edu.et

## VISION

Dire Dawa University aspires to be a premium choice in Ethiopia and among the top ten Applied Science Universities in Africa by 2030.

## በህግ ጥላ ስር ለሚገኙ ታራሚዎች የልብስ ስፌት ስልጠና መስጠት ተጀመረ።











የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በፌደራል ማረሚያ ቤት አስተዳደር በድሬደዋ ማረሚያ ቤት ለሚገኙ 30 ታራሚዎች ነው የልብስ ስፌት ስልጠናው መሰጠት የተጀመረው።

በኢንስቲትዩቱ የቴክስታይልና አፓሬል ፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት አጠቃላይ ቁጥራቸው 30 ለሚሆኑ በህግ ጥላ ስር ለሚገኙ ታራሚዎች የሚሰጠው የልብስ ስፌት ስልጠና ለተከታታይ 30 ቀናት የሚቆይ ነው።

በስልጠናው መክፈቻ ላይ የኢንስቲትዩቱ ሳይንትፊክ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ገዳፋዬ እንዳሉት ዩኒቨርሲቲው በእስከ ዛሬው በማኅበረሰብ አቀፍ አገልግልቱ በርካቶችን ተጠቃሚ ያደረገ ተግባራትን አከናውኗል።

ኢንስቲትዩቱ በቀጣይም በተለያዩ መስኮች ታራሚዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራትን ያከናውናሉ ያሉት አቶ ቴዎድሮስ በተለይም ታራሚዎች የተጣለባቸውን የቅጣት ጊዜ አጠናቀው ወደ ህብረተሰቡ ሲቀላቀሉ ሥራ ፈጣሪ በመሆን ከራሳቸው አልፈው ሌሎችንም መጥቀም እንዲችሉ የሚደረገው ድጋፍና እገዛ ይቀጥላል ብለዋል።


በፌደራል ማረሚያ ቤቶች የድሬደዋ ማረሚያ ቤት ኮምሽን ም/ ኮምሽነር ወንድሙ ደበላ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ከዚህ ቀደምም የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው በተለይም ታራሚዎችን በሞያ ለማብቃት የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ማረሚያ ቤቱ ብዙዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ዩኒቨርሲቲው የበኩሉን ድጋፍ እንዲያደርግ በዚሁ ወቅት ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

በመጨረሻም የዩኒቨርሲቲው የልዑኳን ቡድን በማረሚያ ቤቱ ታራሚዎች እየተከናወኑ የሚገኙ የምርትና የልማት ሥራዎች ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

## Partnership with DDU

A team from the US embassy in Addis Ababa visited Dire Dawa University. A team led by the Regional English Language Officer for africa, Gena Rhoades, visited the university accompanying the newly arriving English Language fellow from the USA. The fellow will stay for months and support the university's ELIC in its service to the academic community. The fellow will also coordinate and support the American Corner in Dire Dawa city.





Dire Dawa University

Address
P.O.B: 1362
Dire Dawa
Ethiopia

International & Public Relation Office:
Tele:
025-111-1501
E- mail: prof-fice@ddu.edu.et

Face book: DDU

Telegram:DDU

## " ዓድዋ፤ የኢትዮጵያ እና የጥቁር ህዝቦች የሉዓላዊነት መገለጫ" በሚል መሪ ቃል 128ኛው የዓድዋ ድል በዓል በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በፓናል ውይይት ተከበረ፡፡



128ኛው የዓድዋን ድል በዓል በማስመልከት የድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረሰብ አገልግልት ዳይሬክቶሬት ከዩኒቨርሲቲው የታሪክና ቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር የፓናል ውይይት ተካሄደ፡፡

በዚሁ በዓል ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የማኅበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ ዲን የሆኑት ዶ/ር መዓዛሽወርቅ እርገጥ ሲሆኑ በንግግራቸው የአሁኑ ትውል የቀደመ ታሪኩን በቅጡ ተረድቶ በዓድዋ ድል የተገኙ የድል ቱሩፋቶች ማስቀጠል እንዲችል ከምሁራን ብዙ እንደሚጠበቅ ገልጸው ለዚህም ኮሌጁ በቀጣይ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ እንቅስቃሴዎችን የሚያርግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ ላይ የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተማም አወል የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም የዓድዋ ድል በዓል ጀግኖች አባቶቻችን በተባበረ ክንድ ወራሪውን የፋሺሽት ኃይል ቅስም በመስበር ድል ነስተው የሀገራችንን ክብር ማፅናት የቻሉበት በዓል መሆኑን አስታውሰው ዛሬም የሀገራችን ጠላቶች ከየአቅጣጫው ተሰልፈው መጠነ ሰፊ የጥፋት ዘመቻ ስለከፈቱብን ሁላችንም ከቀደሙት ጀግኖች አባቶቻችን የተረከብናትን ሀገር ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ከመቼው ጊዜ በበለጠ ክንዳችንን አስተባብረን በአንድነት መቆም ይጠበቅብናል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ በታሪክና ቅርስ አስተዳደር ት/ት ክፍል መምህራን 'Islam-state Relation and the Battle of Adwa (1889- 1896)' በመምህር አብዱልከሪም ተመስገን እንዲሁም 'Adawa Victory Centenary Commemoration: Scholars and Politicians/EPRDF Government Discourses,1996' በመምህር ናትናኤል ለምለም ሁለት ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

## Official Launch of European Union Erasmus+ Project "EtD-Fam- Ethiopian and Djibouti Females at Makerspace"

The Dire Dawa University Erasmus+ project "EtD-Fam- Ethiopian and Djibouti Females at Makerspace" team members travelled to Italy to participate in the official launch of the project. The launch, which happened at the Free University of Bolzano, Italy, brought together researchers from Ethiopia, Djibouti, Germany, Italy and Austria. The project will realize the establishment of makerspace at the Dire Dawa University, which will give female students, staff and others the opportunity to acquire practical skills, competencies. The makerspace will be managed by female researchers and will lead to launch of creative product or business. The makerspace, which will be within the university's Business and Technology Incubation Center, will create an opportunity to establish close cooperation between the university and startups in the city.



